

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የክረምት 2025 እ.ኤ.አ ወቅት አጋማሽ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## እ.ኤ.አ. ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2025 የነበረዉ የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምብረ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+2511115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የክረምት ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

**<u>አጠቃላይ</u>**

ለዘንድሮ የክረምት ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ ከመስጠቱ አስቀድሞ በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ መካከለኛውና ምሥራቃዊ ክፍል ላይ ቀደም ባሉት ወራት የነበረውና በመጪዉ የክረምት ወቅት የሚኖረው የባህር ወለል ሙቀት ሂደት ላይ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናት ተደርጓል፡ ፡ በተጨማሪም የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምሥራቃዊ ክፍል የባህር ወለል የሙቀት መጠን ለውጥን፤ የአሃዛዊና ዳይናሚካል የሞዴል ትንበያዎችን መሰረት በማድረግ በይበልጥ ከመጪው ክረምት ጋር ከፍተኛ መመሳሰል እንደሚኖረው እና ይህንን መሠረት በማድረግ ሁለት ተመሳሳይ ዓመታት ተመርጠዋል፤ እነዚህም እ.ኤ.አ 2006፣ እና 2018 ናቸው።

በክረምት ወራት የፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል የሙቀት መጠን ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ (ENSO Neutral) እንዲሁም የሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ (Neutral IOD) ስር ሆኖ ሊቆይ እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም በህንድና አትላንቲክ ውቅያኖሶች ከፍተኛ የአየር ግፊቶች (High pressure cells) እንዲሁም ሌሎች የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በክረምት ወቅት የሚጠበቀው የዝናብ መጠንና ሥርጭትን አስመልክቶ ትንበያው ተሰጥቷል።

በዚህ መሰረት ባለፉት የክረምት ሁለት ወራት የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን አከባቢዎች ላይ መበደኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ሁለት ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እንዲሁም በግብርናው በዉሃ ሴክተሮች እና በጤና ላይ አሳድሮ የነበረው የዳሰሳ እንዲሁም ወደፊትም ሊፈጥር በሚችለው ተፅእኖ ላይ ጽሁፍ ቀርቧል።

### 1.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በዘንድሮው የክረምት ወቅት የዝናቡ አጀማመር ደቡብ ምዕራብ፤ በምዕራብና መካከለኛው ቀደም ብሎ የጀመረ ሲሆንና፤ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ደግሞ መደበኛ ፈሩን ተከትሎ ጀምሯል፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሁለት ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የዉሃ አካል ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ (ENSO-Neutral) የተስተዋለበት


ሲሆን፣ የህንድ ውቅያኖስ ሰሜናዊዉ ክፍሉ የውሃ አካል በ (Near-neutral IOD) ክስተት ስር መሆኑ ከደቡብ ንፍቀ ክበብ የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው እርጥበት አዘል አየር መጠናከር አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፉት የጁንና የጁላይ የክረምት ወራት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተስተዋለ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎችም ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በ24 ሰዓት ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ በጁን እና ጁላይ ወር በ227 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.1-127 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡


ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺና መተከል ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ ላይ ከ200-1000 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ21-56 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1)፡፡ በተጨማሪም በአርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሀረርጌ ዞኖች፤ የሰሜን ሸዋ ዞን፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቅልበቲ፣ ሃሪ እና የጋቢ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣ ላይ ከ101-350 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ7-20 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1)።

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


ባለፈዉ ሁለት የክረምት ወራት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ክልል የምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ምምራቅ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እሰከ ጁላይ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እሰከ ጁላይ 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እሰከ ጁላይ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የተገኘው እርጥበት በክረምት ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለመኸር የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የጎላ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ በጁን ወር የነበረው እረጥበት በአብዛኛዎቹ የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ መደበኛውን ፈር ተከትሎ የጀመረ ሲሆን፣ የተገኘውም እርጥበት በመጠንም ሆነ በስርጭት አብዛኛዎቹን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ያዳረሰ ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ዉስጥ እርጥበት በማሻሻል ከሰኔ ጀምሮ ለሚዘሩ ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማካሄድም ሆነ ወቅቱን ጠብቆ ዘር ለመዝራት  የሚያስችል ነበረ። በተመሳሳይ ሁኔታም አስቀድመው በበልግ ወራት ለተዘሩና ፍሬ ማፍራት ላይ ለነበሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ ከኤፕሪል ወር ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች የውሀ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉና በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተገኘው መጠነኛ እርጥበት ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረው (ካርታ 4 ሀ )።

በጁላይ ወር የተገኘዉ እርጥበትም ከጁላይ ወር ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ ሰብሎችን ለመዝራትና አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች ለደረሱበት የሰብል ዕድገት ደረጃ የሚያስፈልጋቸውን እርጥበት እንዲያገኙ ያስቻለ ሲሆን እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ  የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ የውሃ ፍላጎትን ለማሻሻል፣ ለግጦሽ ሳርና ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡


በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከፍተኛና ተከታታይነት የነበረው እርጥበት ለጎርፍ መከሰትና በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ መጠነኛ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡

በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በአሪ ዞን ደቡብ አሪ ወረዳ ከመር ቀበሌ የተከሰተው የመሬት ናዳ ለሰው ህወት መጥፋት እና ለንብረት መውደም ሆኗል። በተጨማሪም በረዶ ቀላቅሎ ከጣለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በቅንብቢት እና በመሃል ሜዳ በሰብሎች ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን ከእርጥበት መብዛት ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች የሰብል ማሳዎች መጨቅየትና የአፈር መሸርሸር ክስተቶች የተስተዋሉ ሲሆን፤ በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ በእርሻ ማሳ ላይ ለቀናት ዉሃ የመተኛ ተግዳሮቶች ተስተውለዋል (ካርታ 4 ለ )።

በአጠቃላይ ባሳለፍናቸው ሁለት የክረምት ወራት (ጁን እና ጁላይ) የእርጥበት ሁኔታ በእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ሁኔታ አብዛኛው ለመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አከባቢዎች አዎንታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ በቡቃያ እና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን ሆኖም በወሩ መጀመሪያ ሳምንታት አካባቢ በጥቂት የሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ለግብርና ስራ አንቅስቃሴ በቂ እርጥበት ያልነበረበት ሁኔታ የተስተዋለ ቢሆንም ከቀን ወደ ቀን ግን እየተሻሻለ በመምጣቱ የማሳ ዝግጅት ለማከናወንም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ ነበረው። እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4 ሀ እና ለ)።




ካርታ 4 ሀ እ.ኤ.አ ጁን 2025
የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ





ካርታ 4 ለ እ.ኤ.አ ጁላይ 2025
የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ

### 1.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ

ባለፉት ሁለት  በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ከመጠነኛ  እስከ በጣም ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተለይም በጁላይ ወር በአባይ፣ በባሮ አኮቦ፣ በኦሞ ጊቤ፣ በተከዜ፣ በላይኛው አዋሽ እና በስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶቸ ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ወደ ግድቦች የሚገባው የውሃ ፍስት በመጨመሩ በተለይም በቆቃ፣ በግልገል ጊቤ1፣ በፊንጫ፣ በተከዜ እና በጣና በለስ ግድቦች በዚህ ወቅት ከሚያኙት የረጅም ጊዜ አማካይ የተቀራረበ ዉሃ እንዲይዙ አስችሏል፡፡ በሌላ በኩል በነበረው የገፀ ምድር ውሃ ፍስት እንዲሁም ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በባሮ አኮቦ ተፋሰስ በጋምቤላ፣ በላይኛው አዋሽ ተፋሰስ በአዋሽ በሎ እንዲሁም በአዲስ አበባና  በአንዳንድ የሸገር ከተማ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ ክስተት የነበረ ሲሆን ይህም በንብረት እና በመሰረተ ልማት ላይ መጠነኛ ጉዳት አስከትሏል፡፡ በአጠቃላይ ባሳለፍነው የክረምት አጋማሽ ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ለአብዛኛው የክረምት  ተጠቃሚ ተፋሰሶች የተሻለ የገጸ ምድር የውሀ ፍስት እንዲኖር በማስቻሉ ለኃይል ማመንጫም ሆነ ለመስኖ ግድቦች የተሻለ የውሀ ይዘት እንዲኖራቸው ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው (ካርታ 5 ሀ እና ለ)።




ካርታ 5 ሀ እ.ኤ.አ የጁን ወር የተፋሰሶች የእርጥበት ሁኔታ





ካርታ 5 ለ እ.ኤ.አ የጁላይ ወር የተፋሰሶች የእርጥበት ሁኔታ

## 1.4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁን እና ጁላይ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የምዕራብ፣ የሰሜን አጋማሽ እና የምሰራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለወባ ትንኝ መፈጠርና መስፋፋት ምቹ ሁኔታ እንደነበረ የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የትግራይ ክልል፣ አማራ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ አብዛኛው የጋምቤላ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያና የሲዳማ ክልል፣ አብዛኛው የምዕራብ፣ የምሥራቅ እና የመካከለኛው ኦሮሚያ ክልል፣ የሀረሪ ክልል እንዲሁም በጥቂት የሶማሌ ክልልና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳደር ለወባ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ለወባ ትንኝ ለመራባት የሚያስችል መጠነኛ ምቹ ሁኔታ እንደነበራቸው መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6 ሀ እና ለ)።





ካርታ 6ሀ፣ የጁን ወር ለወባ ትንኝ መራባት የነበረ ምቹ ሁኔታ




ካርታ 6ለ፣ የጁላይ ወር ለወባ ትንኝ መራባት የነበረ ምቹ ሁኔታ

በሌላ በኩል የነበረውን የሙቀት ሁኔታ በሰዎች ጤንነት ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ስንመለከት በተለይም በአፋር፣ በሶማሌ፣ በጋምቤላ፣ በመተከል እና በመተማ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ በሁለተኛው ወር ከአፋር እና ከሶማሌ ክልል በስተቀር በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ላይ አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ በተወሰነ መልኩ እየቀነሰ እንደመጣ መረጃዎች ያመለክታሉ። በአንጻሩ ግን በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባበቢዎች ላይ የነበረው የሙቀት ሁኔታ ለሰዎች ተስማሚ የአየር ሁኔታ እንደነበረ ለማየት ተችሏል (ካርታ 7 ሀ እና ለ)።






ካርታ 7ሀ፣ የጁን ወር የነበረ አስጨናቂ የአየር ሁኔታ (Heat stress)

ካርታ 7ለ፣ የጁላይ ወር የነበረ አስጨናቂ የአየር ሁኔታ (Heat stress)


## 2. እ.ኤ.አ ከኦገስት 1/2025 እስከ ሴፕቴምብር 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በኦገስት ወር በተጠናከረ ሁኔታ ቀጣይነት የሚኖረዉ ሲሆን የወቅቱ የመጨረሻዉ ወር በሆነዉ በሴፕቴምበር ግን ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መዳከም የሚጀምሩበት ነዉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከሴፕተምበር የመጀመሪያዉ ሳምንት ጀምሮ ዝናቡ ከሴሜን ምሥራቅና ከምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀስ በቀስ መልቀቅ የሚጀምርበትና ወደ ደቡባዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስፋፋበት ወር ነዉ፡፡ በአጠቃላይ በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ወር ዝናቡ ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ወር ሲሆን በሴፕተምበር ወር በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የመከሰት ዕድሉ ከፍተኛ ነዉ፡

ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምስራቃዊውና የመካከለኛው ክፍል የባህር ወለል የሙቀት መጠን ከመደበኛ ጋር በተቀራረበ ሁኔታ(ENSO - Neutral) ስር የቆየ ሲሆን በቀሪዎቹ የክረምት ወራትም ቀጣይ የመሆን እድሉ 60% እንደሚሆንና በበጋ ወቅትም ከመደበኛው በታች የመሆን እድል ከ56% እንደሚሆን መረጃዎች ያመላክታሉ። በተጨማሪም የሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት አሁን ላይ በ(Neutral IOD) ስር እንደሚገኝና በቀጣይነት (Neutral-IOD) ሆኖ ይቀጥላል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ሁለት ወራት (ኦገስት እና ሴፕቴምበር) በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተጠናከረ እንደሚሄድ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚፈጠሩ ጠንካራ ደመናዎች ቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች ሙላት ሊያስከትል የሚችል ከባድ ዝናብ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሊዘወተር ይችላል፡፡ የክረምቱ አወጣጥም በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች የሚዘገይ ሲሆን ከአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ደግሞ መደበኛ ፈሩን ተከትሎ እንደሚወጣ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በመሆኑም በቀጣዮቹ ሁለት የክረምት ወራት (ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር 2025)፣ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 4)፡፡ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ነጎድጓድ አዘልና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የወንዞች ከመጠን በላይ መሙላት እንዲሁም ቅጽበታዊ ጎርፍ በረባዳማ ቦታዎች እና ጎርፍ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች ላይ የመከሰት እድል ቀጣይነት ሊኖረዉ ይችላል። ስለሆነም ከጎርፍና ከወንዞች ዉሃ ሙላት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት ዝቅተኛ ስፍራዎችና በወንዞች ተፋሰስ አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰቡ ክፍሎችና የሚመለከታቸዉ አካላት ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እናሳስባለን::




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት1 - ሴፕቴምብር 2025 የሚኖረው

## 2.1 ከኦገስት 1/2025 እስከ ሴፕቴምብር 30/ 2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ሁለት የክረምት ወራት (ኦገስት እና ሴፕቴምበር) የሚጠበቀው እርጥበት በመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለግብርና ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በመኸር ወቅት ለሚመረቱ ለመካከለኛና ረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ዘግይተዉ ለተዘሩ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በሌላ በኩል ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ የሰብል ማሳዎች ላይ እንዳይተኛ ቦይ ማውጣት፣ የማንጣፉፍና የመከላከል ስራ መስራት እንዲሁም አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአንጻሩ በአንዳንድ ቦታዎች በሚኖረው ከባድ ዝናብ እና ተከታታይ የሆነ የዝናብ ቀናት ጋር ተያይዞ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር መሸርሸርና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ለዚህ ስጋት ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት እና ግንዛቤ በማስጨበጥ የአደጋ ተጋላጭነትን እና ሊደርስ የሚችል የተያያዥ ስጋትን ለመቀነስ የሚያስች የተቀናጀ የቅድመ ጥንቃቄ ስራ ከወዲሁ ማከናወን ይመከራል፡፡ በአጠቃላይ በግብርናው ሴክተር ላይ ያሉ የሚመለከታቸው አካላት በቀሪ ሁለት የክረምት ወራት ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል በቂ ዝግጅት በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚስችል ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል።

## 2.2 ከኦገስት 1/2025 እስከ ሴፕቴምብር 30/ 2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የኦገስት እና የመስከረም ቀሪ ሁለት የክረምት ወራት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። ይህም ሁኔታ በተለይም ቀደም ብሎ ከተገኘው የገጸ ምድር የውሃ ሀብት ጋር ተዳምሮ በተፋሰሶች እንዲሁም በተለያዩ ግድቦች ላይ ያለውን የውሃ አቅም የሚያጎለብት

ሲሆን በሌላ በኩል አሁናዊ የውሃ ይዘታቸው በመሙላት ላይ በሚገኙ እንደ ተከዜ፣ ግልገል ጊቤ|፣ ቆቃ፣ የፊንጫ እና የጣና በለስ ግድቦች የቅርብ ክትትል በማድረግ አስፈላጊ የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል። በተመሳሳይ ሁኔታ የደለል ስጋት ያለባቸውን እንደ ግልገል ጊቤ1 እና ቆቃ ግድቦች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ ሊኖር ከሚችለው ተደጋጋሚ ከባድ ዝናብ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ እንዲሁም የወንዞች መሙላት በተለይም በታችኛው የኦሞ ጊቤና የአዋሽ፣ የባሮ አኮቦ ተፋሰሶች በተለይም በወንዝ ዳርቻ፣ በረባዳማ እና ረግረጋማ አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊ የቅድመ የጥንቃቄ ዝግጅት እንዲደረግ ይመከራል። በመሆኑም የዘርፉ አካላት የውኃ ሀብትን ለማጎልበት የሚኖረውን መልካም አጋጣሚ በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም እንዲሁም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት የሚያስችል የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት፣ የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት፣ ፍሳሽ መውረጃዎችን ሊዘጉ የሚችሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ፣ ወራጅ ውኃን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር፣ ለጎረፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች ላይ የቅርብ ክትትል ማድረግ፣ በሌላ በኩል ዉሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና በተገቢዉ ሁኔታ በማጠራቀም በደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያሰፈልጋል።

## 2.3 ከኦገስት 1/2025 እስከ ሴፕቴምብር 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የኦገስት እና የመስከረም ቀሪ ሁለት የክረምት ወራት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሰሜን እና የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ የአየር ጠባይ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህ መሠረትም በቀሪ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ዝቅተኛ እና መካካለኛ ከፍታ ባላቸው በምዕራብ፣ በመካከለኛውና በምሥራቅ ኦሮሚያ ክልል፣ በድሬዳዋ፣ በሀረር፣ በደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ፣ በመካከለኛው ኢትዮጵያ፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአማራ፣ በትግራይ እና በደቡባዊ አፋር ክልል ለወባ እና ተመሳሳይነት ላላቸው በትንኝ ለሚተላለፉ በሽታዎች ምቹ የአየር ሁኔታ ይኖራል። በሌላ በኩል በአብዛኛው የሀገራችን ክፍል ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ስለሚጠበቅ በእነዚህ ቦታዎች ላይ እንደ ኮሌራ ለመሳሰሉ የውሀ ወለድ በሽታዎች የመከሰት ዕድል ስለሚኖረው

የሚመለከታቸው የዘረፉ አካላት እና ማህበረሰቡ ስጋትን እና ተጋላጭነትን የሚቀንሱ ተግባራትን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል። ሆኖም የወባ በሽታ ስጋት ሊኖር የሚችለው በቀጣይ የበጋ ወራት በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ ዝግጅትና ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እንመክራለን። በሌላ በኩል በምስራቅ የሀገራችን ክልሎች ማለትም በአፋርና በሶማሌ እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የዴንጉ ፌቨር በሽታ የመከሰት ዕድል ስለሚኖር በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች እና የሚመለከታቸው አካላት የቅድመ ጥንቃቄ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል።

Ethiopian Meteorology Institute